አንዳችን ለመናገር እጅግ የሚከብደንን ነገር ነፍሳችን ውስጥ እናገኘዋለን (በውስጣችን ይሰማናል)" እሳቸውም፦ "ይህን (በነፍሳችሁ ውስጥ) አገኛችሁን?" አሏቸው። እነሱም፦ "አዎን" አሉ። "ይህ ግልፅ ኢማን ነው።" በማለት መለሱላቸው።

አቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ፦ የተወሰኑ የነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ
ይስፈን ባልደረቦች ወደነቢዩ በመምጣት እንዲህ ብለው ጠየቋቸው፦ " አንዳችን ለመናገር እጅግ የሚከብደንን ነገር ነፍሳችን ውስጥ እናገኘዋለን (በውስጣችን ይሰማናል)" እሳቸውም፦ "ይህን (በነፍሳችሁ ውስጥ) አገኛችሁን?" አሏቸው። እነሱም፦ "አዎን" አሉ። "ይህ ግልፅ ኢማን ነው።" በማለት መለሱላቸው። [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

የተወሰኑ የነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ባለደረቦች ወደርሳቸው በመምጣት አስቀያሚና እጅግ የሚፀየፉት በመሆኑ ሳቢያ ለመናገር የሚከብዳቸው የሆነ ነገር በነፍሳቸው ውስጥ ስለሚከሰት ትልቅ ጉዳይ ጠየቋቸው። ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፦ "ይህ በውስጣችሁ የተሰማችሁ ነገር ግልፅ ኢማንና ሰይጣን በልባችሁ የሚጥለውን ለመከላከል የሚያነሳሳችሁ እንዲሁም በነፍሶቻችሁ ውስጥ እሱን መናገር እንድታወግዙና እንዲከብዳችሁ የሚያደርግ የእምነት እርግጠኝነት ነው። ሰይጣን ልቦችችሁን አልተቆጣጠረምና ነው። ሰይጣን ልቡን የተቆጣጠረው ግን ውስጡ የሚሰማውን እንዳይናገረው የሚከለክለውን አያገኝም።" በማለት መለሱላቸው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/65011